# ምድብ ሁለት (ከ1ኛ — 3ኛ) ክፍል

## 34 ኛ ሳምንት

## ቅዱስ ጴጥሮስ በመልአኩ እርዳታ ከእስር ተፈታ

**ዓላማ**

- ስለ ቅዱሳን መላዕክት ተራዳኢነትና ጥበቃ መማር፡፡

**ምንባብ**

- የሐዋ.ሥ.12÷5-19

**መግቢያ**

- ቅዱሳን ሐዋርያት የክርስቶስን ስምና ስለዕርሱ ሲመሠክሩ በአይሁድና በሌሎች ኢአማንያን ብዙ መከራ ደርሶባቸዋል፡፡
- ዛሬ ከሐዋርያት አንዱ ቅ. ጴጥሮስ እንዴት ለእስር እንደተጣለና በመልአኩ እርዳታ እንዴት? እንደተፈታ እንማራለን፡፡

**የክለሳ ጥያቄዎች**

1. ጌታን የካደው ደቀመዝሙር ማን ነበር? ማንስ ነው እርሱን የተካው?
2. ደቀመዛሙርቱ ስለ ክርስቶስ መስበክ የጀመሩት መቼ ነው?

**ትምህርቱ**

- ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በኂላ መጀመሪያ ማስተማር የጀመሩት በኢየሩሳሌም ነበር፡፡
- የአይሁድ መሪዎች ደቀመዛሙርቱን በማሰርና በመግረፍ ዝም ለማሰኘት ሞክረዋል ፡፡
- አገረገዥው ሄሮድስም ጴጥሮስን አሠረው፡፡ ሌሎቹ ደቀመዛሙርትም ይሄን ሲሠሙ ጴጥሮስ በደህና እንዲፈታ ጸሎት ያዙ፡፡
- በሌሊት ቅዱስ ጴጥሮስ ታስሮ ከሁለት ጠባቂዎች መሐል ተኝቶ ነበር፡፡ በሰንሠለት ታስሮም ነበር፡፡በውጪ ያለውን በር የሚጠብቁ ሰዎችም ነበሩ፡፡
- ሁሉም ተኝተው በእንቅልፍ ላይ ሳሉም መንፈቀ ሌሊት በሆነ ጊዜ በድንገት፤የእግዚአብሔር መልአክ ተገልጦ ነበርና ቤቱ በብርሃን ተሞላ፡፡
- መልአኩ ቅዱስ ጴጥሮስን ቀሰቀሰው ጫማው አድርጎ እንዲከተለውም አዘዘው፡፡ሰንሠለቶቹም ከእጁ ወደቁ፡፡
- ጴጥሮስም መልአኩ እንደነገረው አደረገ፡፡ ጴጥሮስ በሕልሙ ራዕይ የሚያይ ይመስለው ነበር፡፡ሁለቱን የእስር ቤት በሮች አልፈው ወደ ዋናው የእስር ቤቱ የብረት በር ሲደርሱም ተከፈተላቸውና ወጡ፡፡
- ከወጡ በኂላም መልአኩ ተሠወረው ጴጥሮስም ሕልም እንዳልሆነና ጌታ መልአኩን ልኮ እንዳዳነው ተረዳ፡፡
- ወደ ቅዱስ ማርቆስ እናት ማርያም ቤትም ሄዶ አንኳኳ፡፡በዚያም ስለ እርሱ ጸሎት ተይዞ ነበር፡፡
- መፈታቱንም ሲያረጋግጡ በጣም ተደሠቱ እንዴት ጌታ መልአኩን ልኮ እንዳዳነውም ነገራቸው፡፡

**ጥያቄዎች**

1. ጴጥሮስን ያሰረው ንጉስ ማነው?

---

2. በቤተክርስቲያን ቅዱስ ጴጥሮስ እንዲፈታ ይጸለይ የነበረው የት ነው?

---

3. ጴጥሮስን ከእስር ያወጣው ማነው?

---

4. ከእስር እንደ ወጣ ወዴት ሄደ?

---

5. ጴጥሮስ ለምን ታሰረ?

---

**መዝሙር**

ተናገሩ ድንቅ ስራውን መስክሩ(2)
ተጓምሩን ለዓለም ንገሩ(2)
ድንቅ ስራውን መስክሩ(2)

**ይቆየን፡፡**